# አቃተን መማሩ

ትላንት ፣ ዛሬን ወልዳ ፣ ላትመለስ ሄደች
ዛሬም እንደናቷ ፣ ነገን አርግዛለች
ነገም በቀጠሮ ፣ ነገ ፣ ትመጣለች
እሷም እንደናቷ ፣ እሷም እንዳያቷ
አይቀርም ታልፋለች ።

ትላንትና ፣ ዛሬ ፣ ነገ ፣ እየተባለ
አዱ ቀን ፣ ላንዱ ቀን ፣ እያቀባበለ
አልፍ ትላንትና ፣ አልፍ ቀን ፣ ተቆጥሮ
ነገም ፣ ነገ ይመጣል ፣ እንደገና ዞሮ ።

ሺ ዘመን ቆጠርን ፣ ሺ ትውልድ አለፈ
ሁሉም በየተራው ፣ እየተሰለፈ
በዚህ የህልም ፣ ዓለም እየተጠለፈ
ቀንም ሆነ ፣ የሰው ልጅ ፣ ማን አለ ያላለፈ?

ትላንትናም ዛሬም ፣ ዘላለም ላይኖሩ
ዛሬም ትላንት ፣ ሊሆን እያልን ፣ እሹሩሩ
አንደኛው ባንደኛው ፣ እያየን ሲሻሩ
ዛሬን ብቻ ፣ እያየን ፣ አቃተን መማሩ ።

ታዛቢው February 4/2012